# ከጠላትና ከባንዳ ጋር ከመነዳት፤ ቆራጥና ጠንካራ ሆኖ ትግሉን በጥራት

ኃይለ ልዑል ግርማ (ዋሽንግተን ዲሲ)

ከወያኔ የተንኮል ሥራዎች መካከል አንዱ በአምሳያ ከጠፈጠፋቸው ተለጣፊ ድርጅቶች ወይም በተቋቋሙ በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ የራሱን ሰዎች አስርጎ አስገብቶ ሊቆጣጠራቸው ካልቻለ፤ በኢትዮጵያዊነት ላይ የተመሰረቱትን ነጻ የሙያ ማህበራት፣ የወጣቶች፣ የሴቶች፣ ሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የሃይማኖት ተቋማትና ማህበራዊ ድርጅቶችን ሁሉ ለማፍረስ፣ ለማበጣበጥና ለማጥፋት የሚያደርገው የጥፋት ድርጊት ነው። የታወቀው መፈክሩም "ተቆጣጠረው አለዚያ ደምስሰው" ነው።

ወያኔ የፈጠራቸውና "ተቃዋሚ" ብሎ ያስቀመጣቸው ድርጅቶች ለሕዝብ ለማስመሰል እንደልባቸው ይናገራሉ፣ ይጽፋሉ፣ ወያኔን ይተቻሉ ሆኖም ግን የአቋም ጉዳይ ሲነሳ ሰላሳ ምክንያቶችን ደርድረው መንገዳቸውን ከወያኔ ጎራ ሲያደርጉ በተደጋጋሚ አይተናል ታዝበናል።

በምርጫ 97 በተካሄደው የሕዝብ ድምጽ ወያኔ በከፍተኛ ደረጃ ተሸንፎ መዘረሩ ይታወሳል። የሕዝብ ድምጽ ተቀማ ተሰረቀ ተብሎ ተቃውሞ ሲነሳ ግን የወያኔ የውስጥ አርበኞች በእንዴት ዓይነት አካሄድ ትግሉን እንዳኮላሹት ተመልክተናል። ለጊዜው አዲስ ነገር ሆኖ ግራ ያጋባው፣ ለረዢም ጊዜም አለመግባባት የፈጠረው፣ ደጋፊውን ክፍል የከፋፈለውና በሁለት ጎራ ያስቀመጠው፣ አብዛኛውም እቤቱ እንዲከተት ያደረገው በቅንጅት አመራር ላይ የተቀመጡትን ሁሉ መሪዎቻችን ብለን ተቀብለን ሳለ፤ በወቅቱ እንቆቅልሽ ሆኖ ያስቸገረን ወያኔ አስቀድሞ ያስገባቸውን ሰርጎ ገቦች እንዳሉ አለመጠርጠራችንና ያለማወቃችን ነበር።

እነ ልደቱ አያሌው የቅንጅት አመራር ሰርጎ ገቦች እንደነበሩ ደርሶባቸው በወቅቱ ስላገለላቸው ሕዝብ ወዲያውኑ ስራቸውን አውቆ አክ እንትፍ ብሎ ተፋቸው። ሁላችንም እንደምናስታውሰው ልደቱ "ማንዴላ" እየተባለ መጠ ራት ተጀምሮ እንደነበር አይዘነጋም። ዛሬም ከአምስት የማይበልጡ ልደቱን የሚያመልኩ ጓደኞቹ ብቻ ናቸው አብረውት የቀሩት።

የእነ ብርሃኑ ነጋና አንዳርጋቸው ጽጌ፣ የነብርቱካንና ፕሮፌሰር መሥፍን አዲስ የፈለፈሏቸው ድርጅቶችም ሚናቸው ከልደቱ ያልተለየ መሆኑን ብናውቅም ከእባብ እንቁላል እርግብ የሚጠብቁ አልጠፉምና ብርሃኑ ነጋ "ቼ ፈረሴ" እያለ ከሻዕቢያ ጉያ ወጥቶ ኢትዮጵያን ነጻ ሊያወጣ ተነስቻለሁ ሲል የሚያምኑ ጥቂቶች አሉ። እነ ብርቱካንና ፕሮፌሰሩ ደግሞ የአገር ቤቱን ትግል ያዳከሙ መስሏቸው "በሰላማዊ መንገድ" እንታገላለን እያሉ በሌላ በኩል ከብርሃኑ ጋር "አንተ በውጭው በርታ" "እኛ በውስጥ ይዘናል" ይባባላሉ። ዋናው ዓላማቸው በ2010 የሚደረገውን ምርጫ ተሳትፈው እንደ እነልደቱና ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ የፓርላማ መቀመጫ ወንበር ለማሞቅና ከወያኔ ጋር አብሮ ለመሥራት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው። ወያኔ ጠላት አይደለም ሲሉን እኮ ከወያኔ ጋር አብሮ በሰላም መሥራት ይቻላል ማለታቸው ነው። ለዚህም ነው እነ ብርቱካን ሚዴቅሳ ቅንጅት አንስቷቸው የነበረውን የስምንቱን ነጥብ ጥያቄዎች ውድቅ አድርገው ወያኔ በሚሰጣቸው እና በሚያዛቸው መንገድ ለመሄድ የመረጡት። ከዚህ በላይ ቁልጭ ያለ የወያኔ ታማኝ ተቃዋሚነት የትም አይገኝም። አሁን የሁለቱም ክፍሎች አካሄድ ግልጽ እየሆነ በመምጣቱ የኢትዮጵያ ሕዝብም ለነልደቱ የሰጣቸውን የከሃዲዎች ቦታ ለእነርሱም እንደማይነፍጋቸው አረጋግጧል። የእነ ብርሃኑ ነጋና ብርቱካን ሚዴቅሳ ድራማ ተቃዋሚ መስሎ ለማጭበርበር እንጂ ከሕዝብ ከተለያዩና ሕዝብ ጀርባውን ካዞረባቸው ቆይቷል።

ቢሆንማ ኖሮ ወያኔ አገሪቱን በጎሳና በዘር ከፋፍሎ ከሻዕቢያ ጋር የጫጉላ ጊዜ ላይ በነበረበት ጊዜና አሥመራ ከነመለስ ጋር የውስኪ መለኪያ ይዘው ሲያጋጩ በነበረበት ወቅት፤ እነ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ፣ ዶክተር ያዕቆብ ኃይለማርያምና ሌሎችም የወያኔ አጫፋሪዎችን በቴሌቭዥን እና ፎቶግራፎቻቸውን በጋዜጣ ያየንበትን አስታውሰን በቅንጅት አመራር ላይ ጉብ ባሉበት ጊዜ እረ ከዬት መጣችሁ? እናንተ እነማን ናችሁ ?እስከዛሬ ምን ስትሰሩ ከረማችሁ? ብለን አፋጠን መጠየቅና ዞር በሉ ማለት ይገባን ነበር። ሆኖም ግን ወያኔን ለመጣል ከነበረው ከፍተኛ የሕዝብ ጉጉትና እንቅስቃሴ አንጻር እንዲያ ሳይደረግ ቀረና ዛሬ ለዚህ ሁሉ መተራመስና ችግር ተዳረግን። አንድ ሰው ፕሮፌሰር ስለሆነ ዶክተር ስለሆነ ወያኔያዊ ስራ ባንዳዊ ስራ አይሰራም የተባልን ይመስል በያዙት ዲግሪ ስም ተታለንና ተሸንግለን የሕዝባችንን መከራ አራዘምነው። ዛሬ ያ መደገም የለበትም። እነዚህን የወያኔና የውጭ ጠላት መልዕክተኞችን ወጊዱ ብለን ትግሉን ከሕዝባችን ጋር በቆራጥነት መግፋት ብቻ ነው ያለን አማራጭ። ስለሆነም የግንቦት ሰባት ድራማ ተወንያንና እራሱን "አንድነት ለፍትሕና ለዲሞክራሲ"

ብሎ የሚጠራው የነብርቴካን ቡድን ከወያኔ አጫፋሪነት ውጭ ሌላ ሚና ስለሌለው በተደጋጋሚ በመታለልና በየዋህነት ጊዜያችሁን እንዳታባክኑ ማሳሰቡ አይከፋም።

በሌላ በኩል ደግሞ ትላንት የወያኔ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ሆነው፣ ሕዝባችንን በዘር ከፋፍለው፣ አገር አስገንጥለው፣ የተቃወማቸውን አስገድለው፣ በጦርነት ከ70000 ዜጋ በላይ አስጨርሰው ዛሬ ለፍርድ መቅረብ የነበረባቸውን እነ ገብሩ አሥራትን፣ እነ ሰዬ አብርሃን እንደታጋይ በመቁጠር የሕዝብ ትግል እንዲመሩ የሚያመቻቹ የወያኔ ተላላኪዎችን ይህን የጥፋት ሥራችሁን አቁሙ እንላለን። በዋሽንግተን ዲሲና በሌሎች ከተማ ይህን ሲያራግቡ የነበሩ የቴሌቭዥን ጣቢያ፣ የፓልቶክ ክፍሎች፣ የሬዲዮና ተቃዋሚ ነን የሚሉ ደርጅቶች ሰዎች ይህን የሚያሳፍር ወያኔያዊ ስራችሁን ታሪክ በክፉው ገጽታው የማይረሳው ነው እላለሁ።

የወያኔን ሰዎች በየምክንያቱ መድረክ የሚሰጡት ግለሰቦች፣ ስብስቦች፣ የኪነት ሰዎች፣ ፓልቶክ ክፍሎችና ሬዲዮን ጣቢያዎች ሁሉ ጎራችሁ ከወዴት እንደሆነ አውቀናልና በተቃዋሚ ጎራ ስም አትነግዱ ብሎ ማስጠንቀቁ ተገቢ ነው። ተቃዋሚ መስለው ተቃዋሚውን ለመጥለፍና መውጋት ነው ጠጋ ጠጋ የሚሉት።

በዋሽንግተን ዲሲ የተቋቋመው የቴሌቪዥን ጣቢያ (ETN) በነማን እንደተቋቋመ ከታወቀ ሰንብቷል። እነ ብርሃኑ ነጋ፣ ብርሃነ መዋ፣ ሰዬ አብርሃ እና ሌሎችም የወያኔ እና የውጭ ጠላት ቅጥረኞች ንብረት መሆኑን፤ እነ ታማኝ በየነም ታማኝነታቸውን ከወያኔ ጎራ ማድረጋቸውን መጋለጡ ይታወሳል። ዛሬ የቴሌቪዥን ጣቢያው ኃላፊ አቶ ብርሃነ መዋ መሆኑ እንግዲህ ከየትም ተነስቶ እንዳልሆነ ማስታወስ ያስፈልጋል። የጣቢያው ዋና ዓላማም የሕዝብን ትኩረት ማስቀየርና የኪነት ባለሞያዎችን እያግባቡ ለወያኔ እጅ እንዲሰጡ ማድረግ፣ የታወቁ ግለሰቦችን እያቀረቡ "ማኖ" ማስነካት፣ ከትግል መድረክ ይልቅ የንግድ መድረክ ማድረግ መሆኑን ገሃድ እየወጣ ነው። እነታማኝም ስማቸው ከመድረክ ሲጠፋ ምክንያት እየፈለጉ "ከፍተኛ ሰላማዊ ሰልፍ" ይደረጋል ብሎ አንዴ ለድንበሩ ጉዳይ 20 ሰው ለቴዲ አፍሮ ሰድስትና ሰባት ሰው ይዞ በዋሽነግተን ዲሲ ታማኝ በየነ ብቻውን ለቴሌቭዥን ፕሮግራሙ ዝግጅት እራሱን ማቅረቡ የሚገርም አይሆንም። በ10 ሺዎች የሚቆጠር ሕዝብ በሚወጣበት ዋሽንግተን ዲሲ እነታማኝ የከሸፈ ድራማቸውን ለማሳየት 7 ሰው ይዘው ሲወጡ ከሕዝብ ምን ያህል እንደራቁም ያሳያል።

ስንቱ ጋዜጠኛ እውነትን በመዘገቡ ብቻ በህይወቱ ሲከፍል፣ ሲታሰር፣ ሲደበደብ፣ በገንዘብ ሲቀጣና ከአገር ሲሰደድ፣ የወያኔ ቃል አቀባዩ አማረ አረጋዊ የፕሬስ ነጻነት ያለ ለማስመሰል ሪፖርተር የሚለውን ጋዜጣ እያተመ ድራማ ሲሰራ ቆይቷል። ዛሬ ጎንደር ደርሶ ስለተመለሰ እንደ ታጋይ ተቆጥሮ አብይ ዜና መሆኑና በየፓልቶኩ ቃለ መጠይቅ ሲደረግለት መስማት እጅግ ያሳዝናል ያሳፍራልም። እስከመቼ በወያኔ አክሮባቲስቶች ድራማ ሲሰራብን እንታለላን? አማረ አረጋዊ ለፍርድ እንጂ ለቃለመጠይቅ እንግድነት ማቅረብ የማይገባ ነው።

ዞሮ ዞሮ ትግሉ አቅጣጫ እንዲስት ስለሆነ የሚፈለገው ምድረ ባንዳና አንጃ ሁሉ አርዕስት እየፈጠረ በየመድረኩ አለን አለን የሚሉት ሕዝብ እንደተፋቸው በመገንዘባቸው ስለሆነ በድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ስም የሚራወጡት ሰዎች ዓላማችሁ ታውቋልና የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ከነዋሪው ሕዝባችን በላይ የሚያውቀው የለምና ሰላሳ ዓመት በላይ ውጭ የከረመ ሰውን የድንበር ጉዳይ ኤክስፐርት ነው እያሉ በማቅረብ ድንበራችንን የሚያስመልሱ የሚመስሉትን ሁሉ አርፈው ቢቀመጡ ይሻላል።

ጊዜው ሕዝባችን በረሃብ እየረገፈ፣ በከፍተኛ የኢኮኖሚ ውድነት የሚበላው እያጣ መቸገሩን፣ ጭቆናና አበሳው እየከፋ መሄዱን ስንረዳ በእውነተኛ የሕዝብ ፍቅርና ስሜት በአገር ንጹሕ እርዳታና የጠራ አቋም ይዞ መታገል እንጂ ወያኔ ባዘጋጀልን የትግል መስመር ወይም ባቡር ላይ ተሳፍረን ገደል ሲገባ አብሮ መግባት ሲያዞረን አብረን መዞር የለብንም።

ያገር ቤቱን ትግል ለማገዝና የወያኔን የደም ሥር ለመዝጋት እዚህ ዋሽንግተን ዲሲ የጀመርነውን የወያኔን ሸቀጥና አገልግሎት ያለመግዛትና ያለመጠቀም አድማም መልካም ይዟል እንበርታ፤ ጎረቤታችን ካናዳም ውስጥ መጀመራቸውን አሳውቀዋል ዓለም አቀፍ ማድረጉ ደግሞ የሁላችንም ወቅታዊና አጣዳፊ ሥራ ነው እላለሁ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!